# ዘላቂ መፍትሄ ለትኩስ ሀይል

**ንግስት ፍስሀጺዮን**

**12-24-16**

**(zqueenofmom@gmail.com)**

ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ በርካታ ተግባራትን እያከናወነች ትገኛለች። በሌላ በኩል ገጽታዋን ለማጥፋትና ስሟን ለማጉደፍ፣ እድገቷን ወደኋላ ለመጎተት፣ ስኬቶቿን በማራከስ ገጽታዋን ለማቆሸሸ የሚሯሯጡ ወገኖች አሉ። ከዚህ በተጨማሪ በመንግስት በኩል አንዳንድ የሃገሪቱን ገጽታ የሚያበላሹ ሁኔታዎች ለመከላከል ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አካሄድ ላይ ድክመት መኖሩን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች አሉ።

የሃገሪቱን መልካም ገፅታ እያበላሹ ካሉ ችግሮች መሃከል ልመናና የጎዳና ተዳዳሪነትን በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። መንግስት ለነዚህ ችግሮች እልባት እየሰጠ እንደሆነ በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች በየጊዜው ሲገለጽ ቆይቷል። የተከናወነውን ስራ ከውጤት አኳያ ስንመዝነው ግን ከሚነገረው በተለየ መልኩ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ እንዳልሆነ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች አሉ። እንደ ትርፍ ስራ እየታየ ያለና ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ ቋሚ ምፍትሄ እየተበጀለት አለመሆኑን የሚያሳዩ ሁኔታዎች አሉ።

ሰዎች  ለልመናና ጎዳና ተዳዳሪነት የሚዳርጓቸው የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች ናቸው። ድህነትና ኋላ ቀርነት፣ ድርቅ የሚያስከትለው የምግብ እጥረትና ጦርነት፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች፣ ወረርሽኝ፣ የአካል ጉዳት፣ በትዳር መፍረስ ምክንያት የቤተሰብ መበተን፣ በተለያየ ሱሶች መጠመድ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ለልመና ገሚዳርጉ ቀውሶች መሃከል ተጠቃሾቹ ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በሊጋሽነት የሚመዘገቡ ወይም ለዕርዳታ እጃቸውን የሚዘረጉ ተቋማትና ግለሰቦች መበራከት የጥገኝነት መንፈስን በማበረታታት ልመና እንዲጠናከር ያደረገበት ሁኔታ መኖሩን የሚጠቁሙ እውነታዎች አሉ፡፡

በመዲናችን አዲስ አበባ የሚገኙ የጎዳና ተዳዳሪዎችና ለማኞች በአብዛኛው ሙሉ አካልና መስራት የሚያስችል አቅም ያላቸው ናቸው። በወጣትነት እድሜ ክልል ያሉትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ይሁን እንጂ በአመዛኙ ሰርተው የመኖር ፍላጎት የላቸውም። ይህ የሆነው ሰርተው ከሚያገኙት በተሻለ በምጽዋት የሚያገኙት ገቢ የተሻለ ሆኖ መገኘቱ ነው። ይህ ሁኔታ የአዲስ አበባ ብቻ ሳየሆን የተቀሩት የሃገሪቱ ትላልቅ ከተሞችም ገጽታ እየሆነ መጥቷል። ይህ ጽሁፍ በስራ አጥና ድጋፍ ፈላጊ ወጣቶች ላይ ያተኩራል።

የሀገራችን ወጣቶች ባለፉት ስርዓቶች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽና የማራመድ፣ በነጻ የመደራጀትና የፖለቲካ ተሳትፎ ማደረግ የማይችሉበት እንዲሁም ስር የሰደዱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች የተተበተቡበት ሁኔታ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ የኢፌዴሪ ስርአት የወጣቶን ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች በህገመንግስት አረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶች በስራ ፈጣሪነት

ተደራጅተው ወደስራ እንዲገቡ የፋይናንስ፣ የመስሪያ ቦታና የሞያ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በተለይ ከ3ኛው ሃገራዊ ምርጫ በኋላ በ1998 ዓ/ም በተዘጋጀው የወጣቶች የልማትና ተጠቃሚነት ፓኬጅ በግል እና በህብረት ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ከምንም ተነስተው በሚሊዮን የሚቆጠር ሃብት ማፍራት የቻሉ፣ የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ህይወት በማሻሻል እንዲሁም በስራቸው ላሉ ወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

የወጣቶች የልማትና ተጠቃሚነት ፓኬጅን ተግባራዊ በማደረግ እንቅስቃሴም በርካታ የአገራችን ወጣቶች ተጠቃሚ መሆን መቻላቸው እየታየ ነው። ለዚህ ጽሁፍ አስረጅ ይሆን ዘንድ የአዲስ አበባ ወጣቶችን ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነታቸውን እና የማህበራቸውን እንቅስቃሴ እንመልከት።

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ለበርካታ የወጣት ማህበራትና መሰል አደረጃጀቶች መሰረት የጣለ ማህበር ነው። የከተማዋ ወጣቶች በሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን መሪ ተሳትፎ ያጐለበተ፤ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ፤ ስነ-ልባናዊና ፖለቲካዊ ችግሮቻቸውን በራሳቸው ጥረትና በባለድርሻ አካላት ድጋፍ መቅረፍ እንዲችሉ አደራጅቶ ያነቃነቀ ከሁሉም አቻ ማህበራት ተጠቃሽና ውጤታማ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር በ2008 ዓ/ም ያከናወናቸውን ተግባራት ስንመለከት፤ በስራ እድል ፈጠራ 5ሺ 113 ስራ አጥ አባላቱን በተለያዩ ቋሚና ጊዜአዊ የስራ አድሎች ተጠቃሚ አድርጓል። ለ11 ሺ 484 ወጣቶች ከስራ ማማረጥና መናቅ አመለካከት የጸዱ እንዲሆኑ ማድረግ የሚያስችል ስልጠና በመስጠት መቅረፍ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የስራ ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ አስችሏል።

የተመቻቸላቸውን እድል በመጠቀም ወደ ስራ ገብተው ከተለወጡት ወጣቶች በተቃራኒ ቁርጠኝነት በማጣት፣ የሚገባውን ያህል ትኩረት ስላልተሰጣቸው፣ ከሱስ መላቀቅ ከብዷቸው አሁንም በሱስ እና በጎዳና ህይወት ላይ ህይታቸውንና አቅማቸውን እያበላሹ የሚገኙ ወጣቶች ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

ከአለም አቀፍ ድርጅቶች የሚወጡ ጥናታዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአለም አቀፍ ደረጃ በአደገኛ ዕጽ ምክንያት በየደቂቃው ሶስት ሰዎች ህይወታቸውን ያጣሉ። ከዚህ ባሻገር የአደገኛ ሱስ ተጠቃሚዎች በአካባቢያቸው ለሚኖሩ 10 ሰዎች የጤና መጓደል ምክንያት ናቸው፡፡ ከሌሎች ሀገሮች በበለጠ በአደገኛ ዕጾች ተጠቃሚነት ምክንያት የሚመጡ ችግሮች በአፍሪካ ጎላ ብለው ይታያሉ፡፡ እ.ኤ.አ በ2013 በወጣው የአለም ጤና ድርጅት ሪፖርት መሠረት በአፍሪካ ከአጠቃላይ ህዝቡ 50 በመቶ ወጣት ሲሆኑ 22.7 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በአደገኛ እፅ ሱሰኝነት የተጠቁ ናቸው፡፡ ወደ ሀገራችን ስንመጣ ከጠቅላላው ህዝብ 30 በመቶ ወጣት ክፍል መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በቁጥር ምጣኔ ረገድ ካላቸው ከፍተኛ ድርሻ ባሻገር ወጣቶች የብሩህ አእምሮ፣ የእምቅ እውቀትና ጉልበት ባለቤት ናቸው። እነዚህ ወጣቶች ሃገር የመረከብና የሀገሪቱን ህዳሴ በጽኑ መሰረት ላይ የማቆም ሃላፊነት የጠብቃቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የክልል ከተሞች የጎዳና ላይ ህይወትን እና ደባል ሱሶች ውስጥ የተዘፈቁ ወጣቶች ቁጥር ቀላል አይደለም።

በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ የጎዳና ተዳዳሪዎች ቁጥር 150 ሺህ መሆኑን ያመለክታል። የዕርዳታ ድርጅቶች መረጃ በአዲስ አበባ ብቻ የጎዳና ተዳዳሪዎች ቁጥር 100 ሺህ እንደሚደርስ ያመለክታል፡፡ በክልል ከተሞች ያሉትን ሲጨምር ቁጥሩ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ማለትም 600 ሺህ እንደሚደርስ የተባበሩት መንግስታት አመልክቷል። ይህን ሃገራዊ ችግር በዘላቂነት መፍታት የሁሉም ህብረተሰብ ኃላፊነት ቢሆንም ዋናው ግን መንግስት ነው። መንግስት በጉዳዩ ላይ አሁን እየሰራ ካለው የበለጠ በርካታ ስራዎችን ይጠበቁበታል።

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋውን የሪፎርም ትግበራ ኘሮግራም መሠረት በማድረግ በርካታ ተግባሮችን ማከናወናቸውን ከቀረቡት ሪፖርቶች መረዳት ይቻላል። ሚኒስቴሩ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት መዘርጋትን በተመለከተ በ2007 በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ931 ሺህ 693 በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች (አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች፣ ቤተሰብ፣ ህፃናት ወዘተ) እንክብካቤና ድጋፍ ለመስጠት አቅዶ፣ ለ678ሺህ 335 (ወንድ 291ሺህ 744፣ ሴት 269ሺ ህ131፣ ፆታ ያልተገለፀ 117 ሺህ 460) የህብረተሰብ ክፍሎች የአመራርና የምክር፣ የሙያ ስልጠና፣ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ ድጋፍና የማቋቋም አገልግሎቶች ሰጥቷል። አገልግሎቱን ካገኙት መካከል 150 ሺህ 263 አረጋውያን፣ 25ሺህ 556 ጐዳና ተዳዳሪዎች፣ 6 ሺህ 332 ሴተኛ አዳሪዎች፣ 122 ሺህ 503 አካል ጉዳተኞች፣ 7 ሺህ 17 ለምኖ አዳሪዎች፣ 235 ሺህ 317 ህፃናትና ቤተሰብ እንዲሁም 131ሺህ 347 ሌሎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች መሆናቸውን አሳውቋል፡፡ ይህ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ተግባር ነው።

ሀገራችን ሰላም በማረጋገጥ ወደ የልማትና እድገት ጎዳና ጉዞ ላይ ትገኛለች። በአንድ ወቅት ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ‹‹የሚሰሩ እጆች እያሉን፣ ትኩስ ሀይል እያለን ለልመና እጃችንን አንዘረጋም።›› የሚል ንግግር ማሰማታቸው ይታወሳል፡፡ ልክ ነው፤ ልመና በተለይም በወጣትነት እድሜ ላይ ሲሆን ችግሩን የከፋ ያደርገዋል በሀገር ላይ የሚያደርሰውም ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ቀውስ ከባድ ነው፡፡

የሰራተኛና ማህበራዊ፣ ስፖርትና ወጣቶች ፣ ሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴሮች፣ ከኤልሻዳይ በጎ አድራጎት ማህበር እንዲሁም ከዩኒሴፍ በመተባበር በጎዳና ላይ የሚኖሩ ፍቃደኛ ወጣቶችን በመመልመል በመጀመሪያው ዙር 10ሺ ወጣት የጎዳና ተዳዳሪዎችን በአዋሽ ሰባት የመከላከያ ማሰልጠኛ ስልጠና ወስደው በተለያዩ ሙያዎች ስራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ በሁለተኛ ዙር ሌሎች 10ሺ የሚሆኑ የጎዳና ወጣቶች ተመልምለው 5ሺ የሚሆኑት በግብርና ዘርፍ በመሰማራት ህይወታቸውን እየለወጡ ይገኛሉ፡፡

መንግስት ምንም እንኳን የጎዳና ወጣቶችን በመሰብሰብ በትራክተር፣ በግብርና እና በተለያዩ ሙያዎች በማሰልጠን ላይ ቢገኝም፣ ችግሩን ግን ከመሰረቱ ማጥፋት አልተቻለም፡፡ በቅርቡ የ2009 ዓ.ም የምክር ቤት የመክፈቻ ላይ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ባደረጉት ንግግር ለወጣቶች የስራ ፈጠራ 10 ቢሊዬን ብር ተዘዋዋሪ ፈንድ መያዙን አስታውቀዋል። ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው በዚህ ፈንድ ስራ እንዲፈጥሩ ዝግት እየተደረገ ይገኛል። ወጣት በሚለው ዝርዝር ውስጥ ያሉ የጎዳና ወጣቶችን፣ በሱስ ችግር ውስጥ የተዘፈቁ ወጣቶችን ትኩረት የመስጠቱ ጉዳይ ግን አሁንም ሊታሰብበት ይገባል።

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎረሜሽን ዕቅድ ለወጣቶች ትኩረት ተሰጥቶ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ተግባሩ ተጀምሯል፡፡ ለአብነት ያህል የወጣቶችን ብቃትና ተጠቃሚነት ከማሳደግ ጋር በተያያዘ የድህረ-2015 የልማት አጀንዳ ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ግቦች ሀገራችን ለዘርፉ ካስቀመጠቻቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥመው ተፈፃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 7.43 ሚሊዮን ወጣቶች በአነስተኛና ጥቃቅን፣ 1.35 ሚሊዮን ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዷል፡፡ በሌላም በኩል 2.5 ሚሊዮን ወጣቶች የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ 12.5 ቢሊዮን ብር እንዲቆጥቡ ለማስቻል፣ 2.19 ሚሊዮን ወጣቶ 10.98 ቢሊዮን ብር የብድር

አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግም ታቅዷል፡፡ ለወጣቶች በቋሚነት በየአካባቢው የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች የሚመቻችላቸው ሲሆን፣ ለ2 ሚሊዮን ወጣቶች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ይህም በአጠቃላይ ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ያላቸውን ድርሻ አሁን ከሚገኝበት 59 በመቶ ወደ 90 በመቶ የማሳደግ ግብ ተቀምጧል፡፡ በተመሳሳይ 4.32 ሚሊዮን ወጣቶች በግብርና 3.64 ሚሊዮን ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ በአሁኑ ወቅት ያለውን 10 በመቶ የወጣቶች ተጠቃሚነት ወደ 30 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ባለፈ ሁሉም ተቋማት የሚሰሯቸው ተግባራት ላይ የወጣቶችን ተጠቃሚነት በማካተት ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ፣ መንግስትና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሱስ ተጠምደው ለውጥ ማምጣት ላየቻሉና ጎዳናን ቋሚ መኖሪያቸው ላደረጉ ወጣቶች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ካሉበት አስከፊ ሁኔታ ሊያወጧቸውና ሊታደጓቸው ይገባል፡፡ ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ ክልሎች ቀደም ሲል የአዲስ አበባ የወጣቶች ማህበርን ስናነሳ እንደተመለከትነው እንደጠቀስነው፣ የወጣት አደረጃጀቶችን በአግባቡ በማዋቀርና መደገፍ፣ በማህበራዊ ደህንነት ችግሮች ዙሪያ ከሚሰሩ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላት እና የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመተባበር የሃገሪቱን የሰው ሀይል በአግባቡ መጠቀም  ይገባል፡፡ ለዚህም ጎዳና ላይ ለወጡ ህፃናትና ወጣቶችም ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ መታሰብ የኖርበታል።